11ኛ ዓመት ቁጥር 1
11 th Year No.1

ባህርዳር ጥር 17 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar January 25,2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 6.75
Unit price

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 120/1998 ዓ.ም
የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

Content

Proclamation No. 120/2006
The revised Amhara National regionalstate Excutive organs Re-establishment, organization and determination of their poweres and Duties proclamation

አዋጅ ቁጥር 120/1998 ዓ.ም

የተሻሻለውን የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣

በህገ-መንግስቱ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በተሟላ ሁኔታ ለማሳካትና የማስፈፀም አቅምን ለማጕልበት ይቻላቸው ዘንድ በሥራ ላይ ያሉትን የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋም አደረጃጀታቸውን መርምሮ ማሻሻልና ስልጣንና

Proclamation No, 120/2006

A Proclamation Issued to Provide for the Re-establishment and Organization of the Revised Amhara National Regional State Executive Organs and Determination of their Powers and Duties

WHEREAS, it is necessary to re-establish the existing National Regional State Executive Organs, by examining and amending their organizational status, and determine their powers and duties with a view to enabling them fully realize the mission entrusted to them b the Constitution and build the executive capacity of same thereof;

ተግባራቸውን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

በሥራ ላይ ባለው አደረጃጀት የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አባላት ከሆኑት አስፈፃሚ አካላት መካከል አንደኛው ለሌላኛው ተጠሪ ሆኖ እንዲዋቀር መደረጉ ለተጠያቂነት ያልተገባ መደራረብ ምክንያት ሆኖ ከመቆየቱም በላይ ለርዕሰ መስተዳድሩ ብቻ ተጠሪ መሆን ያለባቸውና እኩል ደረጃ ያላቸው ቢሮዎችም ሆኑ የበላይ ኃላፊዎቻቸው በሕገ- መንግስቱ መሰረት በምክር ቤት አባልነታቸው ሳቢያ ያላቸውን የጋራ ኃላፊነት የሚያናጋ ከመሆኑ የተነሳ ይህንኑ አርሞ ህጋዊ አቋማቸውን ተመሳሳይ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is nmecessary to rectify and make executive organs similiar in legal status due to executive organ members within the existing organization of the Council of the Regional Government are strcutred in such a way that one is accountable to the other, and this has, thus , resulted in unnecessary overlap of accountability and infurtherance it would distort the joint responsibility that bureaux and their respective hands, owing equal status and accountibility to hand of the government only, have been enterusted by being member of the council pursaunt to the constitution.

ቢሮዎች ሲደራጁም ሆነ የተወሰኑ አስፈፃሚ አካላት ከእነርሱ ጋር በተጠሪነት መስመር እንዲያያዙ ሲደረግ እያንዳንዱ መ/ቤት የተሰጠውን ተልዕኮ የሥራ መጠንም ሆነ ውስብስብነትን እርስ በርስ ያላቸውን ተግባራዊ ተዛምዶ በውል አጥንቶ የም/ቤቱን አወቃቀርና የየርከኑ አስፈፃሚ አካላት የሥራ ግንኙነት ይበልጥ ውጤታማና በተራዘመ ቢሮክራሲያዊ ሰንሰለት ያልተተበተበ ሆኖ መስራት የሚያስችለውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, when bureaus are organized and certain executive organs be accountable to them, it is appropriate to create conducive situation, by properly studing the mission gives to each executive organ, amount as well as complexity of work and the real relationship each other the organs,with a view to enabling the strcture of the council and work relation of Executive organs at all levels operate throe.

በየደረጃው ለሚገኙ የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶችም ሆነ የበላይ ኃላፊዎቻቸው የሚሰጣቸው ስያሜ ወጥነት ያለውና ተገልጋዮችን የሚያበረታታ ሆኖ እንዲቀረፅ ከማድረግ ጐን ለጐን እስካሁን ድረስ በበርካታ ማሻሻያዎች ተበታትነው የሚገኙትን የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያና ማደራጃ ህግጋት ለአሰራር ምቹ በሆነ መንገድ አጠቃሎና አዋህዶ ማውጣት ተገቢ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is proper to uniformly design the designation given to executive organs of all levels of the Regional Government and their respective Heads so as not to confuse service seekers, and in line with this to collectively and all together issue the executive organs establushment and organization laws which are found scattered with several amendments, in a manner suitable for operation;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ- መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Sub- Article 3/1/of Article 49 of the Revised Constitution of the National Region.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

Part One

1. **አጭር**

ይህ አዋጅ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 120/1998 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ቢሮ" ማለት የክልል መስተዳድር ም/ቤት አባል ሆኖ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ወይም በሌላ ሕግ የሚቋቋም የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ አስፈፃሚ መ/ቤት ነው፡፡
2. "የቢሮ ኃላፊ" ማለት የዚሁ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሆኖ እንዲያገለግል በሕገ-መንግስቱ መሰረት የተሾመ ወይም የሚሾም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡
3. "ምክር ቤት" ማለት የብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሲሆን እንደተገቢነቱ የየርከኑን አስተዳደር ም/ቤቶች ይጨምራል፡፡

ክፍል ሁለት
ስለርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

3.ስለርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

የአማራ ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 60 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

4. ስለምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 61 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

5. ስለምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ይሆናል፡፡

General

1. Short title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional state Executive Organs, Re-establishment Organization and Determine of their Powers and Duties Proclamation No.120/2006."

2. **Definitions**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. "Bureau" means the executive body of the national Regional state established as member of the Council of the Reional Government as per this proclamation or to be established by other laws.
2. "Bureau Head" Means any natural person appointed or to be apponinted pursuant to the constitution, to serve as Bureau Head.
3. "Council" means the council ot the National Regional Government and includes adminstrative Council of all levels as deemed appropriate.

PART TWO
Head and Deputy Head of the Regional Government, and the Council of the Regional Government

3. Powers and Duties of Head of the Regional Government

Head of the Government of the Amhara National Region shall have the Powers and Duties provided in under Provisions of Article 60 of the Revised constitution of the Region.

4. Powers and Duties of Deputy Head of the Regional Government

Deputy Head of the Government of the Amhara National Retion shall have the powers and duties provided in under provision of Article 6 of the Revised constitution of the Region.

5. Powers and Duties of the council

The council of the Amhara National Regional Government shall have the peers and duties provided in under provision of Article 58 of the Revised Constitutie of the

6. **የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት**
1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. ርዕሰ መስተዳድሩ፣

ለ. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ስር የተመለከቱትን ቢሮዎች የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎች፣
መ. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣናት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሐ ድንጋጌ ሥር የተመለከተው ማንኛውም የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ በፅሁፍ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል የቢሮው ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

7. **ስለ ክልል መስተዳድር ም/ቤቱ ጽ/ቤት**

1. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ጽ/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ሥር የተመለከተው የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

2. የጽ/ቤቱ ኃላ በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የሚሾም ሆኖ፡

ሀ. የካቢኔውን ጉዳዮች በበላነት ይፈፅማል፣
ለ. በም/ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ያለ ድምፅ ይሳተፋል፣ ሃሳብና አስተያየትም ይሰጣል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የተደረገገው ለበታች የአስተዳደር ጽ/ቤቶችም ሆነ ኃላፊዎቻቸው በተመሳሳይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

8. ስለምክር ቤቱ የመሰብሰቢያ ጊዜ፣ የስብሰባ ስነ-ሥርዓትና አመራሩ፣
   1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት1-
      ሀ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፡፡
      ለ. ምልአተ-ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ውስጥ ከግማሽ በላየ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ

Region.

6. **Members of the Council of he Regional Government**
1. The council of the Regional Government shall have the memers stated herein below:
a. Head of the Regional Government
b. Deput of Head of the Regional Government
c. Heads who oversee bureux indicated under Article 10 of his proclamation.
d. Other officials assigned by had of the regional Government

2. Whenever any one of the Bureau heds indicated under sub-Article (c) of his Article is unable to present at a meeting of the Council, the Deputy Bureau Head with seniority shall, unless the forner represent a participant in writing take part in the meeting of the Council.
7. **The office of the Council of the Regional Government**
1. The office of the council of the Regional Government shall be the office of Head of the Regional Government as indicated under sub-Article 2 of Article 62 of the Revised Constitution of the Region.
2. Head of the office of the Council of the Regional Government. Appointed with bureau head title, shall:

a. Direct over the implementation of the cabinet affairs;
b. Participate in the Council's meeting without casting a vote; give suggestions and comments, however.
3. The provisions provided in under sub-Articles 1 and 2 of this Article hereof shall. Mutatis mutandis. Apply for subordinate administrative offices.
8. **Meeting time procdure and Leadership of the Council**
1. The council of Regional Government shall
   a. Hold regular and extraordinary meetings as partriculars determined by a regulation.

ሲገኙ ይሆናል፡፡

ሐ. ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው በተባበረ ድምፅ ይሆናል በተባበረ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ ግን ጉዳዩን በድምፅ ብልጫ ይወስናል፡፡

2. የክልል መስተደድር ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፡-

ሀ. ለምክር ቤቱ አጀንዳ ሆነው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፡፡

ለ. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣

ሐ. ለምክር ቤቱ አጀንዳ ሆኖ የቀረበ ማናቸውም ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቁሚ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል

3. ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

9. ስለምክር ቤቱ ቁሚ ኮሚቴዎች፣

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

2. የቁሚ ኮሚቴዎች ስልጣንና ተግባራት ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

ክፍል ሦስት
ስለቢሮዎች በጠቅላላው
10.መቋቋም

የሚከተሉት ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1. የአቅም ግንባታ ቢሮ
2. የትምህርት ቢሮ
3. የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ
4. የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ
5. የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ
6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
7. የጤና ጥበቃ ቢሮ
8. የፍትህ ቢሮ
9. የአስተዳደና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ

b. Constitute a quorum in presence of more than half of its members.

c. Constitute a quorum in presenece of more than half of its members

d. Pass decisions unammously; where this may not be possible, the decision shall be decided by majority vote.

2. Without prejudice to the right sof the Council members to propose agendas. Head of the Regional Government shall;

a. Decide on issues to be agendas of the council.

b. Preside over the meetings of the Council.

c. Posipone the meeting of the Council to another time where any is proposed as an agenda to the Council get dectned necessary to be concerned by the concerned standig committee of the Council.

3. In absence of Head of the Regional Government, the Deputy Head shall preside over meetings of the council.

9. **Standing Committees of the Council**

1. The council of the Regional Government, with a view to discharging its powers and duties, shall have various standing committees in whiich members of the Council are incorporated.

2. The powers and duties of the standing committees shall be determined by a directive to be issued by the Council.

PART THIREE
THE BUREAUS
10. Establishment

The following bureaus are hereby established by this proclamation

1. Capacity Building Bureau
2. Education Bureau
3. Agriculture and Rural Development Bureau
4. Trade and industry Burau
5. Public Works and Urban Development Bureau
6. Finance and Economic Devlopment Bureau
7. Health Bureau
8. Justice Bureau

10.የማስታወቂያ ቢሮ
11.የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ
12.የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ
13.የሴቶች ጉዳይ ቢሮ
14.የባህልና ቱሪዝም ቢሮ
15.ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

11.የቢሮዎች የወል ስልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ ቢሮ፡-

1. በሥራው መስክ፡-

ሀ. የፌዴራሉን መንግስት ፖሊሲዎች መሠረት ያደረጉና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ህግጋትን ያመነጫል፣ የሥራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

ለ. የፌዴራሉንና የክልሉን መንግስታት ህጎች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ ያውላል፣

ሐ. ለፆታ እኩልነት መርህ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሴቶችን ህገ-መንግስታዊ ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፣

መ. የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃወችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለሚመለከታቸውመ ያሰራጫል፡፡

ሠ. እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ የራሱን የበታች አደረጃጀቶች ይፈጥራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ መሰል አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡለትም ለብሔረሰብና ለወረዳ አስተዳደሮች ተገቢውን ድጋፍና የምክር አገልግሎት የሰጣል፡፡

ረ. በሕግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ ስምምነቶችን ደርጋል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ወየም በየማቋቋሚያ ህጐቻቸው በተደነገገው መሠረት ተጠሪዎች የተደረጉለትን አስፈፃሚ አካላት አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ሥራዣውን ያስተባብራል፣ አደረጃጀቶቻቸውንና የሥራ ኘሮግራሞቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የክልሉ መንግስት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፡፡

9. Administration and Security Affairs Bureau
10. Information Bureau
11. Water Resource Development Bureau
12. Youth at... I sports Affairs Bureau
13. Women’s Affais Burau
14. Culture and Tourism Bureau
15. Labour and Social Affairs Bureau

11. Collective powers and Duties of Bureaus

Each Bureau shall

1. In its field of activity:

a. Produce region wide politices Strategies and laws based on the Federal state politics and related to the regional objective conditions; prepare plan of work and executiion budget; implement same up on approval:
b. Implement the laws of the Federal and Regional states in the Region:
c. Ensure Constitutional benefits of women by providing special attention to the principle of gender equality.
d. Carry out research activities, collect, organize, and thereby distributes data to the concerned bodies:
e. Create, as deemed necessary, its Subordinate organs in the Region; follow up and supervise their works provide appropriate support and advisory services to Nationality and Woreda adminstrations upon required submitted to it that such organs to be established for them.
f. Eneter into contracts, sue be sued and own property pursuant to law:

2. Direct over and coordinate the performance of executive bodies accountable to a pursuant to article 29 here of, or provisions of their establishments: examine their organiziational structures and activity programs, and decide submission of same to the concerned body or the Regional

3. ተጠሪዎች የተደረጉለት መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች ቢኖሩ በሕግ መሠረት ይቆጣጠራል፣ የልማት አጋዥ ሆነው መሰረታቸውን ያረጋግጣል፡፡
4. በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጐች የተሰጡትን ዘርዝር ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፡፡
5. ስለስራው ክንውን በየወቅቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ዘገባዎችን ያቀርባል፡፡

12.የቢሮ ኃላፊች ተጠሪነትና ኃላፊነት

እያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ፡-

1. ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፣
2. የሚመራውን ቢሮ ይወክላል፣ ስልጣንና ተግባራቱን በሥራ ላየ ያውላል፣
3. ለቢሮው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣
4. በቢሮው ውስጥ ውጤታማ የሥራ አመራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

13.የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተግባር፣

1. እያንዳንዱ ምክትል የቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሚመለከተው ቢሮ ኃላፊ ሆኖ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
2. የቢሮ ኃላፊው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፡፡
3. በማናቸውም ቢሮ ውስጥ የሥራው መጠንና ውስብስብነት ጠይቆ ከአንድ በላየ የሆኑ ምክትሎች በሚገኙበት ጊዜ የቢሮ ኃላፊው በተለይ የፅሁፍ ውክልና የሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር እርሱን ተክቶ ቢሮውን የሚመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል የቢሮ ኃላፊ ይሆናል፡፡

ክፍል አራት
የቢሮ ዝርዝር ስልጣንና ተግባር

Goverment.

3. Control, in accrodance to law public enterprises that may be accountable to it; and thereto ensure that whether they are operating as supportive for development.
4. Implement detailed powers and duties enterusted to it as per this proclamation and other laws.
5. Submit periodically activity reports to Head of the Regional Government and Council regarding its work performance.

12. Accountability and Responsibility of Bureau Heads

Each Bureau Head shall:

1. accountable to Head of the Regional Government and to the Council;
2. Represent the bureau he directs; implement powers and duties entrudted to the bureau;
3. Effect expenditure on the basis of approved budget and work program;
4. Follow up and ensure that the effective manageral system is devised and implemented in the bureau.

13. Accountability and Duties of Deputy Bureau Heads

1. Every Deputy Bureau Head shall be accountable to the concemed Bureau Head and Carry Out activities specifically assigned to him.

2. Act on behalf of the Bureau Head in his absence or under the circumstance where he is unable to perform his norm,al duties.

3. Where there are more than one deputy bureau heads in any bureaus as the volume and complexity of work required, and unless confirmed other wise that there is a person the BureauHead particulary represents in writing the deputy bureau head with pricesppointment shall direct the bureau representing the bureau head.

PART FOUR

14.<u>የአቅም ግንባታ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች የተወሰነው ወይም ወደፊት የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉን ዘላቂ የልማት አቅጣጫ መሠረት አድርጐ በየጊዜው የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን በማጥናት ይለያል፣
2. ለክልሉ ሁለንተናዊ ልማትና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መፋጠን የሚረዱ የማሻሻያ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች በተቀናጀ ሁኔታ መቀረፃቸውንና መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
3. በክልሉ ውስጥ የተለያዩ የማሻሻያ ኘሮግራሞችን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣
4. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ዘመናዊና የተሟላ የሰብአዊ ሃብት አመራር፣ ሥልጠናና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋቱንና በተግባር ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣
5. ለክልሉ ዘላቂ እድገት አስፈላጊነት ያላቸው ተቋማት በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲቋቋሙ፣ በአደረጃጀትም ሆነ በአሠራር እንዲጠናከሩና በሚገባ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
6. በክልሉ ውስጥ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

15.<u>የትምህርት ቢሮ</u>

በሌሎች ህጐች የተወሰነው ወይም ወደፊት የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ትምህርትን በክልል አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀርሳል፣ ለተግባራዊነታቸውመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
2. በሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት የክልሉን ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ስልጠና እቅድና ኘሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

Detalled powers and Duties of Buraux

14. Capacity Bullding Bureau

Without prejudice to previous or forth coming provisions by other laws, the Regional Bureau of capacity Building shall pursuant to this proclamation, have the following detailed powers and duties.

1. Study and identify, based on the sustainable development direction of the region, capacity gaps observed each time.
2. Follow up and supervise that reform programs and projcts helpful for enhancing all round developments and building up of democratic system of the Region are designed and implemented in integration;
3. Formulate general follow upsupervision and evaluation systems with a view to making effective the execution of various reform programs in the region; implementation of same thereof,
4. Ensure whether modern and complete human resource management training, and implemented in the regional civil Service.
5. Cause, upon studies, the establishment, organizational as well as operational strength and proper use of institutions which are important for sustainable development of the region
6. Facilitate conditions for expansion and consolidation of utilization of information and communication technology in the Region.

15. Education Bureau

Without prejudice to previous or forthcoming provisions by other laws, the Bureau of Education shall, Pursuant to this proclamation. Have the following detailed powers and duties:

1. Devise systems enabling promotion of education region-wide, facilitate conditions for their implementation;
2. Prepare primary cycle teachers training plan and program or Regional education

3. በክልሉ ውስጥ ለትምህርት የደረሱ ህፃናት የመማር እድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል መሠረተ- ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡
4. የክልሉን የትምህርት ጥራት በሀገር አቀፍ የተወሰነውን ስታንዳርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣
5. የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ ስታንዳርድ በመከተልና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ የክልሉን የአፀደ ህፃናት፣ የጐልማሶች፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ሥርዓተ-ትምህርት ያዘጋጃል፣ በማንኛውም ደረጃ የሚዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርትም ከሀይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከትና ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
6. በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣
7. መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፣ መብትና ጥቅማቸውም መከበሩን ያረጋግጣል፣
8. በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎችን ተከታትሎ ይፈፅማል በክልሉ ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችና የምስክር ወረቀት ብቃት ያረጋግጣል፣
9. ለትምህርቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ መፅሀፍትና ሌሎች የትምህርት መማሪያዎችእንዲሟሉ ያደርጋል፣
10. የክልሉን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም አስቀድሞ የተቀቋቋሙትንና ወደፊት የሚቋቋሙትን የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እና መሰል ተቋማት ያደራጃል ያስተዳድራል፣
11. በሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና ድርጅቶች ለሚቋቋሙና እስከ ሁለተኛ ደረጃ ለሚደርሱ ትምህርት ቤቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ የብቃት

pursuant to the national education and training policy, implement same upon approval;

3. Devise strategies which enable the provision of the educational opportunities to all school age childeren of the region; and provide basic education to all;
4. Ensure that the quality of education provided in the Region compley with the approved nation standard;
5. Prepare and implement, following the country's education policy standard, and having regard to the objective reality of the Region, the curriculum of kindergarten, adults education elementary schools and teacher training institutions, ensure the curriculum prepared at any level the curriculum prepared at any level is free from religious, political outlook and cultural influences;
6. Ensure taht the qualifying standards to each in each level have been met.
7. Train and cause the training of teaching and education personnel; cares the observance of the rights and Benefttie of same;
8. Follow up the execution of internal examination provided in the school ot the region, ascertain the squency of examinations and certificttee preomed and given at the Regional level;
9. Ensure the provision of bodies and other materials necessary to undciate educational works;
10. Organic and adminstrer elementrary and secondary school as well as teacher trauning colleges and similar institutions established previously and inthe future;
11. Issue license to schools up to secondary

ደረጃቸውን ይቆጣጠራል፣

12. ትምህርትን በጥራት ለማስፋፋት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል ይህንንም የሚያግዙ ኘሮጀክቶች አዘጋጅቶ በስራ ላየ እንዲውሉ ያደርጋል በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
13. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በቁጥር አናሳ ለሆኑ ብሔረሰቦች፣ ለሴቶች ለህፃናት ለጐልማሶችና ለአካል ጉዳተኞች በቂርቡ የትምህርት አገልግሎቶች ረገድ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
14. የክልሉ የትምህርት ኘሮግራሞች በመገናኛ ዘዴዎች እንዲነድፉ ያደርጋል፣
15. የትምህርት ነክ መረጃዎችን ይሰበሰባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣
16. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ስራዎችን ያቅዳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
17. ለተማሪዎች የሚሰጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚጠናከሩበትን ስልት ይቀይሳይ ያስተባብራል፣
18. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን መሠረት አድርጐ ህብረተሰቡ በመማር ማስተማሩም ሆነ፣ በትምህርት አመራሩና አስተዳደሩ ሂደት እንዲሁም በግንባታ ስራዎች ረገድ በስፋት የሚሳተፉበትን ስልትና የአደረጃጀት አግባብ ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም በቅርብ ይከታተላል፡፡

16. <u>የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣</u>

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገውና ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

level by domestic organizations and investors: supervise same to ensre that they maintain edequate standards.

12. Undcrtake studied to enable the expansion of educational quahty prepare and implement projects assisting such studies provide the necessary support to stidies undertaken at the national level;
13. Provide special support, in cooperation with the concerned organs, to educational services rendered to minority nationalities women. Children and adults;
14. Ensure the eduacation program of the Region is supported by educational mass media:
15. Collect, compile and disseminate to the concerned bodies, statistical data on education.
16. Plan construction works necessary for educational purposes, and implement same upon approval.
17. Devise strategies and thereby coordinate same in order to strengthen various services to be rendered to students.
18. Devise strategies and organizational systems, in line with the educational policy with a view to strengthening extensive community participation in learning-teaching process, educational management and adminstration, and construction works; follow up the implementation of same.

16. **Bureau of Agriculture and Rural Development**

Without prejudice to previous and forthcoming provisions by other laws, the Regional Bureau of Agriculture and Rural Development shall, pursuant to this proclamation, have the following detailed

1. በክለሉ ውስጥ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርናና የገጠል ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
2. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ህጐችን ያዘጋጃል አፈፃፀሞቻችን ይከታተላል ያስተባብራል፡፡
3. የምግብ ዋስትና ኘሮግራሞችን በበላይነት የመራል ያስተባብራል፣
4. ለገበሬዎች የሚሰጡ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣
5. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውሃ እቀባና የመስኖ ልማት ስራዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል ድጋፍ ይሰጣል፣
6. ከሚመለከታቸ አካላት ጋር በመተባበር የገጠር መሠረት ልማት አገልግሎት እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
7. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎቶች ለገበሬወች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
8. በግብርናው መስክ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች የተሟላ ድጋፍ ይሰጣል፣
9. በግብርና ልማት ላየ ተፅእኖ የሚኖራቸውን ወቅታዊ ሁኔታዎች ይከታተላል፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ይዘረጋል፣
10. ወደ ክፍሉ በሚገቡና ከክልሉ በሚወጡ እፅዋት፣ አዝርእት፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ላይ ተገቢውን የካራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፣
11. እንስሳትና የዕፅዋት በሽታዎች ወረርሽኝና ተዛማች ተባዮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
12. የግብርና ልማት በገቢያ እንዲመራና ቀልጣፋ የግብርና ግብአትና ምርት የግብይት ስርዓት እንዲፈጠር ለማድረግ ይቻል ዘንድ፣

powers and dutie:-

1. Cause the expanmsion of rapid and sustainable agricultural and rural development in the Region.
2. Prepare in collaboration with relevant Bodies Draft laws on the conservation and utilization of forest and wild life resources in the region follow up and coorednate the implementation of same thereof
3. Oversee and coordinate food security programmes:
4. Encurage and assist the provision of Agricultural extension services to peasants.
5. I encurage and provide support tp collaboration with relevant bodies or the texpansion of water harvesting and irrigation development activates.
6. Facilitate conditions in collecaboration with the concenerend bodies for the expanstion of rural development infrastructure services;
7. Facilitate, in collaboration with relevant bodies, the provision of credit services to peasants.
8. Provide comprehensive support to privaee development and set up all carly Warning system;
9. Monitor events affecting agriculture Development and set up all cary Warning system.
10. Take necessary measures enabling to
11. Take necessary measures enabling to prevent the outbreak o animal and plant Diseases and migratory pests:
12. With a view to enhancing market led agriculture development and creating efficient agricultural inputs and products marketing system:

A. Closely monitor market signals,in particular those of natural and international markets

ሀ. ገበሬዎች እና በግብርና ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶች በዋጋና በጥናት ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን ምርቶች መለየት እንዲችሉ የገበያ ሁኔታወችን በተለይ ሀገር አቀፍና የዓለም ገቢያዎተን በቅርብ እየተከታተለ የተሚላ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

and provides pasents and investors with Comprehensive. Up-to-date Accurate information to enable them identify to those agriculturalproduce which they can produce of competitive price and quality

ለ. ዋና ዋና የግብርና ምርቶችና ግብዓቶችን አስመልክቶ የገቢያ ፍላጐት ትንበያ ጥናት ያካሂዳል፣

B. Conduct demand forecast studies regarding major agriculture products and inputs.

ሐ. ለግብርና ግብዓቶች ግምገማና እፅድቆት የሚረዱ መመሪያዎችንና የአሠራር ስርዓቶችን ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

C. Issue guidelines and producedures for agricultural input evaluation and release and monitor their implementation thereof.

መ. ማናቸውመ የግብርና ግብዓት ጥራቱ ተጠብቆ ለተጠቃሚዎች መሠራጨቱን ያረጋግጣል፣

D. Ensure that any agricultural input distributed to users is upto its quality.

ሠ. የግብርና ግብዓት አመራረት፣ አቅርቦት፣ ሥርጨትና ግብይት አቅምን ለመገንባት አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣

E. Make the necessary support in building the capacity of producing supplying, distributing and marketing agricultural inputs;

ረ. በክልሉመ ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ምርቶች ገበያ የሚስፋፋበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

F. Devise mechanisms for promoting agricultural product markets at the Regional as well as national level and implement same thereof;

ሰ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የግብርና ግብይት አማካሪ ም/ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

G. Facilitate conditions, in collaboration with the concerned bodies, for the establishment and consolidation of agricultural products market centers; cause the establishment of advisory council for agricultural marketing and provide support thereto:

ሸ. የግብርና ምርቶች የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርቡበትን ስርዓት ይፈጥራል፣

H. Create a system whereby the provision of agricultural products for markets are upto their quality standard;

ተ. የግብርና ግብዓቶችን የሚያመርቱ፣ የሚያቀርቡና የሚያሰራጩ አምራቾችና ነጋዴዎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን መስፈርቶች ያወጣል፣

I. Set criteria to be fulfilled by producers and traders engaged in the production, supply and distrbution of agricultural inputs:

በ. አስተማማኝ የግብርና ምርቶች አቅርቦትና ቀጣይነት ያለው ገበያ ይኖር ዘንድ በኮንትራት የማምረት ሥርዓት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣

J. Encourage the expansion of out growers scheme to secure reliable supply of agricultural products and sustainable market:

13. ለግብርናና ለገጠር ልማት እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን መንገድ ያመቻቻል፣
14. የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጅን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ተቋማትንና ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ይመራል፣
15. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሰብል፣ የእንስሳትና የገጠር ቴክኖሎጅ ብዜት ማዕከላትን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ አዳዲሶችም እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣
16. በምርምር የተገኙ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ያቀርባል፣ ያላምዳል፣ ኘሮቶታፖችን ያመርታል፣ ቴክኖሎጂውን በስፋት ለሚያመርቱትም ያሰራጫል፣
17. የሰፈራ ኘሮግራሞችን በማስፈፀም ረገድ ወረዳዎችን ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

7. የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ የንግድ ፖሊሲና ህግ መሠረት መመራቱን ይከታተላል፣ ተገቢነት የሌላቸውና ህጋዊ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እንዳይካሄዱ ይቆጣጠራል፣
2. በክልሉ ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች የሚሰማሩትን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በንግድ ህግ መሠረት ይመዘግባል ፈቃድ ይሰጣል፣ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል ይቆጣጠራል፣
3. በክልሉ ውስጥ የመሠረታዊ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶች ስርጩትን በተመለከተ አግባብነት ባለው አካል የተወሰነው የዋጋ ተመንና የጥራት ደረጃ መከበሩን ያረጋግጣል፡፡
4. ከሌሎች ክልሎ ጋር የሚደረገው የንግድ ልውውጥ የሚስፋፊበትንና የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

13. Identity bottlenecks for agricultural and rural development and thereby facilitate ways towards their solutions:
14. Established and direct training institutions and centers that assist the enhancement of agriculture development ad the improvement of rural technology.
15. Expand and administer crops, anmals and rural technology multiplication centers found in the Region; and cause the establshment of new centers.
16. Provide and adapt new research finding technologies produce protoypes and disseminate same to those widely produce the technology.
17. Coordinate and assist woredas regarding the implementation of settlement programmes.

7. **Trade and Industry Bureau**

Without prejudice to previous or forthcoming provisions by other laws Bureau of Trade and industry shall pursuant to this proclamation, have the following detailed powers and duties

1. Supervise that trade activities undertaken in the Region are directed in accordance with the country's trade policy and law control that unfair and illegal trade activities not to be undertaken
2. Register, pursuant to law and thereby issue license to doestic
3. Ensure the observance of prices and quality standard fixed by the appropriate organ regarding the distribution of basic vommrtvisl goods and services in the Region
4. Facilitate conditions for the expansion and development of trade exchanges undertaken with other Regions;

5. የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል ያስተዳድራል፣
6. የገበያና የንግድ ሥራ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማጠናቀርና በማሰራጨት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
7. በክልሉ ውስጥ የንግድ ምክር ቤቶችና የዘርፍ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጠል፡፡
8. የጠቅላላ ጥራት አሰራርና አስተዳደር እንዲሁም በድርጅቶች መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የሥራ ቁርኝት አሠራር ያስተዋውቃል፣
9. በሀገሪቱ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ መሠረት የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሃሳቦችን በየጊዜው እያመነጨ በፌዴራሉ መንግስት ሊጠኑና በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን በመለየት ለነግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፣
10. በክልሉ ውስጥ በግሉ ኢንቨስትመንት፣ በጥንቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች እንዲሁም በተራንስፖርት አገልግሎት መስኮች የሚከናወኑትን ተግባራት በበላይነት የመራል፣ ይከታተላል፣

18. **የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣**

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገወ ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዘርዝር ስልጣንና ግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የሀገሪቱ የህንፃ ኮድ፣ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ስራ ደረጃዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፡፡
2. በክልሉ መንግስት በጀት ለሲሩ የመንግስት ኮንስትራክሽኖች የሚያስፈልጉ የዲዛይኖችና የኮንስትራክሽን ስራ ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣
3. በክልሉ መንግስት በጀት የሚከናወን ማናቸውም የመንግስት ኮንስትራክሽን በተገባለት ውል

5. establish and administer commercial register of the Region:
6. Provide the necessary support by collecting, organizing and disseminating information on market and trade activities.
7. Encourage and provide support to the estagblishment of chambers of commerce and sectorial associations in the Region;
8. Promote general quality operation management as well as working relationship to be created among organizetions on agreements.
9. Generate periodically, pursuant to the investment policy and law of the country, industrial project proposals and thereby identify and transfer to the ministry of trade and industry those which be studied and implemented by the federal Government;
10. Oversee and follow up activities of private investment, small scale and micreo trade and industry enterprises as well as functions undertaken in the field of rtansport services in the Region.

18. **Bureau of Works and Urban Development**

Without prejudice to previous of forthcoming provisions by other laws, Bureau of Works and Urban development shall pursuant to this proclamaton, have the following detailed powers and duties.

1. Ensure that the country's hodlding codes and standards fr design and construction works are respected within the Region.
2. Cause the preparation of designs and contract documents necessary for government constructions to be financed by the budget of the Regional State.
3. Cause the presence of a controlling system which enables to easure that the

መሠረት የጥራት ደረጃው የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል በበላይነት ይቆጣጠራል፣

4. በከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ ኢንቨስትመንትም ሆነ በከተማ ቦታና የኮንስትራክሽን ስራዎች ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
5. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ የግል ኪራይ ቤቶች ግንባታ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣
6. በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ስር የሚገኙ የከተማ ቤቶተን በሚመለከት ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፣
7. ለከተሞች ኘላን ዘግጅት የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው የፌዴራሉ መንግስት አካላት ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፣ የከተሞችን ኘላን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ኘላኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የከተሞችን ደረጃ በየጊዜው እያጠና ይወስናል፣
8. የከተማው ነዋሪ ህዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ ቤቶችን ሰርቶ ይጠቀምና የመጠለያ ችግሩ ይቃለልለት ዘንድ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣
9. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፊ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፣
10. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች በበጀት ፣ በእቅድና በከተማ ኘላን አዘገጃጀትና አፈፃፀም በሰው ኃይል ስምሪት፣ በአስተዳደርና ገቢ አሰባሰብ ረገድ የከታተላል፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

execution of government constructions undertaken by the budget of the Regional State are in conformity with the quality standards, times and cose limits, as provided in their cofntract: and make over all supervision thereof;

4. Facilitate and provide the necessary cooperation for investement undertaken in towns as well as for construction activities carried out in urban lands;
5. Issue licenses, in cooperation with the concerned bodies, to private rental house constructions undertaken in urban areas.
6. Render technical support concerning urban houses which are under the ownership of the Regional State:
7. Undertake studies that assist the preparation of town planning; make the necessary coopration with concerned bodies of the Federal Government; cause the preparation of detailed plans necessary for the implementation of town planning follow upand suprvise the execution of same; study and decide standard of towns based on periodic studies:
8. Create conducive conditions for urban dwellers so that they may be able to construct and use dwelling houses compatible with their own standards and thereby alleviate their shelter problemes:
9. Encourage the establishment of housing cooperatives; devise ways for providing assistance to them:
10. Follow up and render technical support to lown administations and municipalities in the Region with regard to the preparation and execution of their budget, action plan and urban planning, alloecation of man power, administration and collection revenues:

11.የክልሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበ የኮንስትራክሽንና የመጠለያ ልማት ስትራቴጅ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ይቆጣጠራል፣

12.የከተማ ልማት እንቅስቃሴው ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል ተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፣

13.ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሁምሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣

14.ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተሞች ልማት መስክ የማሰልጠኛና የምርምር ተቋማትን ያቋቁማል፡፡

19. ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሀገሪቱ ልማት ስትራቴጂ ላይ የተመሠረተ በክልሉ መንግስት የሚፈፀም አጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላላ፡-
2. ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር በረጅ/፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ እቅዶች ውስጥ የሚንዘባረቁና በክልሉ መንግስት የሚከናወኑ ኘሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይገመገማል፣

11. Prepare construction and shelter development strategies pertaining to the objective conditions of the Region; implement and supervise same upon approval:

12. Carry out studies so as to inegrate urban development activities with poverty reduction; provide support for the implementation of same;

13. Provide multipurpose and integrated support in order to make towns centers of development in their surroundings;

14. Provide capacity building assistance so as to make urban centers improve their service delivery; where deemed necessary, establish traming and research institutions in the field of urban development

19. Finance and Economic Devlopment Burau

Without prejudice to previous or fothcoming provicions by other laws. Bureau of Finance and Economic Development shall, pursuant to this proclamation, have the following detailed powers and duties.

1. Prepare, on the basis of the country's development strategy, short, medium and long term development plans to be implemented by the Regional Government and upon approval, follow up the implementation of same;
2. Cause the study and preparaton, in coopration with the concerned organs of the Regional State, of projects reflected in the long. medium and short term plans to be executed by the Regional Government: and evaluate same thereof:

3. በክልሉ መንግስት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትንና በመደበኛ በጀት የአገልግሎት እቅዶች እንዲሁም ዓመታዊ የልማት እቅዶችና ለእነዚሁ የሚያስፈልጉ የካፒታል በጀት ጥያቄዎችን መርምሮ የተጠቃለለ አመታዊ በጀት ያዘጋጀል ከአስተያየቱ ጋር ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ የተፈቀደውንም በጀት ያስተዳድራል፣

4. የክልሉ መንግስት አካላት የሀገሪቱን የፋይናንስ ፖሊሲዎች፣ ህጐች ደንቦችንና መመሪያዎተን ተከትለው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል፣

5. የክልል መንግስቱን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልሉ መስተዳድር ምር ቤት ያቀርባል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ በጀት አቅርቦ የስወስናል።

6. አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከማናቸውም የገቢ ምንጭ የሚገኘው የክልል መንግስቱ ገቢ በሚገባ መወሰኑን፣ መሰብሰቡንና ሃሳቡም መያዙን ያረጋግጣል፣ የክልሉ የገቢ መሠረት የሚስፋፋበትና ፍትሃዊ የገቢ አሰባሰብ ስርዓት ተቀረፆ በሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

7. የክልል መንግስቱን የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ይመሰርታል፣ በክልሉ መንግስት አካላት በስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣

8. የክልሉን መንገስት ከሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች የሚያገኛቸውን ብድሮች አስመለክቶ በክልሉ መንግስት ስም ውሎችን ይፈርማል፣ ብድሮተን እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፣

9. የክልለ መንግስቱን የእቃና የአገልግሎት ግዥና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፣

3. Prepare a consolidated annual budget by reviewing the annual production and service plans as well as annual development plans and capital budget proposal necessary there to as prepared and submitted to it by the organs of the Regional Satate and to be implemented by regular budget; submit such consolidated plan and capital budget with recommendations to the Council of Regional Government, and administer the approved budget thereof.

4. Supervise the complication of the operationsof the organs of the regional state with the Financial policies, laws, regulations and directives of the country.

5. Submit periodic general statements to the council of the regional state; where deemed necessary budget.

6. Enusre the proper assessment , collection and recording of revenues of the regional state from any sources as provided by the appropriate laws; facilitate conditions for designing and implementing equitatble system of revenue collection with a view expanding the Regional revenue bases

7. Establish the accounting system of the Regional state, supervise the implementation of same by the organs of the Regional state, and inspect the accounts of same:

8. Sign in the name of the Regional state regarding loan agreements obtained from domestic sources: supervise and administer such loans:

9. Prepare directives concerning procurement and utilization of supplies and survives of the regional state: supervise the im[lementation of same thereof:

10. በሌላ በኩል የመንግስት አካል ስር የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የክልሉ መንግስት ንብረት ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል፣
11. ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አስተገባበር አንፃር በክልሉ ውስጥ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጭ የሆነ አመለካች እቅድ ያዘጋጃል፣
12. የክልሉ የረጅም ፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ለማዘጋጀት የሚረዳ የኢኮኖሚ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የኘላን ሜትዶሎጅና አጠቃላይ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ መለኪያዎችንና መመዘኛዎችን ያዘጋጃል፡፡
13. ከፌዴራሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚተላለፉለትን የኘላን አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያዎተን ለክልሉ አሠራር አመቺ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ ከማብራሪያ ጋር ለክልሉ መንግስት አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፣
14. የክልሉን የተፈጠሮ ሀብት የምርት የስነ-ህዝብ የሳይንስና ቴክኖለጅ ስርጭትና የአገልግሎት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸውም ያስተላልፋል፣
15. ለክልሉ ልማትና እድገት የሚያስፈልጉ የቅየሳ የካርታና የጅኦግራፊ ጥናት ስራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
16. የየሴክተሩን እቅድ አፈፃፀም እየገመገመ በየሩብ አመቱ የተቀናበረ ሪፖርት ለክልሉ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣
17. የሀገሪቱ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
18. በስነ-ህዝብና በልማት ሁኔታ ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ በክልሉ ውስጥ የስነ-ህዝብ ፖሊሲን በሚመለከት የሚካሄዱ ምርምሮች እንዲበረታቱ ያደርጋል ለፖሊሲው ተግባራዊነት እንደአስፈላጊነቱ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ተግባራቸውንም ይከታተላል፣
19. ህዝብና ልማትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤትና ለሚመለከተው የፌዴራል መንግስት አካል ያስተላልፋል፣
20. <u>የጤና ጥበቃ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

10. Be responsible for and administer the property of the Regional state which is not administered or utilized by any other organ of the regional state:
11. Prepare indicative plns with a view to

1. በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡
2. የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የክልሉን ህዝብ ጤና የሚጠበቅበትን እቅድና ኘሮግራም ያዘጋጀል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣
3. ለህዝብ ጤና አጠባበቅ የወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራዡውን ያረጋግጣል፣
4. የክልሉን ነዋሪ ህዝብ ፍላጐት መሠረት በማድረግ በየደረጃው የጤና ድርጅቶችን የጥናትና ምርምር ማዕከላትንና የማሰልጠኛ ተቋማትን ያደራጃል ያስተዳድራል፣
5. በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድሃኒቶችንና የህክምና መሣሪያዎችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፣
6. በሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና ድርጅቶች ለሚቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች ክሊኒኮች፣ የምርመራ ድርጅቶችና መድሃኒት ቤቶች ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን መስፈርት ጠብቀው መሰራታቸውን ይቆጣጠራል፡፡
7. በክልሉ ውስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማማላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣
8. በክልሉ ውስጥ የሚያገለግሉ መለስተኛና መካከለኛ የጤና ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣
9. ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድሃኒቶችና የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊው ህክምና ጋር ተዋህደው በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡ ባለሙያዎችን ያደራጃል ያበረታታል፡፡
10. የጤና ፖሊሲውን መሠረት አድርጐ የክለሉ ህዝብ በሽታዎችን በመከላከል ላየ በስፋት የሚሳተፍበትን ዘዴና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡
11. ለጤና አገልግሎት መስፋፋት አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ስራዎችን ያቅዳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
12. የህዝብን ጤና ለመጠበቅ በሚደረገው የኳራንቲንግ ቁጥጥር ይሳተፋል፡፡
13. በምግብ እጥረት ወይመ አለመመጣጠንና ብክለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የማያግዙ ስልቶችን ይቀይሳይ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ የምግቦችን ለጤና ተስማሚነት ያረጋግጣል፡፡

21.የፍትህ ቢሮ

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወየም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ፍትህ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉተ ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የክልሉ የፍትህ አስተዳደር ስርዓት የሚሻሻልበትን መንገድ ያጠናል፣ በአግባቡ ተደራጅቶ ለክልሉ ነዋሪ ህዝብ ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
2. የህግ ጉዳዮችን በሚመለከት የክልሉ መንግስት አማካሪ ሆኖ ይሰራል፣
3. በክልሉ ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር በሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች የክልሉን መንግስት በመወከል ይከራከራል፣
4. የየደረጃውን አቃቢያነ ሕግ በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል፣
5. በማረሚያ ቤት፣ በማረፊያ ቤት፣ በጠባይ ማረሚያና በጊዜያዊ የእስረኞች መጠለያ የሚገኙ ሰዎች በአግባቡ መያዛቸውንና ህጋዊ መብታቸውን መከበሩን ያረጋግጣል፡፡
6. በክልሉ መንግስት ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡ በህግ መሠረት የወንጀል ክስ ያነሳል፡፡
7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል መንስኤዎተን ያጠናል፣ ለወንጀል መከላከል የማረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ወንጀል የሚቀንስበት ስልት ይቀይሳል፡፡
8. የወንጀል ድርጉት ምስክሮች እንደአስፈላጊነቱ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፣
9. በወንጀል ድርጊት ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸው በክልሉ ፍርድ ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች ካሣ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ክስ ሊረዳ ይችላል፣
10. የእያንዳንዱ መ/ቤት የመንግስትና የህዝብ መብትና ጥቅም የማስከበር ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝቡን እንዲሁም የክልሉን መነግስት መብትና ጥቅም ለማስከበር በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባኤ ክስ ይመሰርታል፡፡ እንዲመሰረት ያደርጋል ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፡፡
11. የክልሉ መንግስት ወይም አካላቱ ተከራካሪ

የሚሆንባቸውን የፍትሐብሔር ክሶችና የመብት ጥያቄዎተን አያያዝ እንደ አስፈላጊነቱ ይከታተላል፡፡ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንደያቀርብለት ያደርጋል ለዚህም ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፡፡

12. በክልሉ መንግስት ወይም በአካላቱ ጥያቄ ሲቀርብለት የህግና ደንብ ረቂቆችን በማዘጋጀት ይረዳል፣
13. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትርፍ ላይ ያልተመሰረተ ዓላማ ይዘው የተቋቋሙና በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ማህበራትንት ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሰርዛል ይቆጣጠራል፣
14. በክልሉ መንግስት ፍ/ቤቶች መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣
15. ከሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ አንፃር የህዝብን ንቃተ-ህግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የህግ ትምህርት ይሰጣል፣ የህግ ትምህርትና ስልጠናን በሚመለከት አግባብ ካላዠው አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፣
16. የክልሉን የኮዲፊኬሽንና ህጐችን የማጠቃለል ስራ ይካሄዳል፡፡
17. በክልሉ ውስጥ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤቶች እንዲደራጁ ያደርጋል ስራቸውንም በበላይነት ይመራል፣
18. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ ዳኞች፣ አቃቢያነ ህግ፣ የፖሊሲ አባላትና እንደአስፈላጊነቱ ለሌሎች ባለሙያዎች የስልጠና ኘሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ስልጠና ይሰጣል፣
19. ለማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች እንዲሁም ለባህላዊና ልማዳዊ የዳኝነት አካላት አስፈላጊውን ስልጠና ይሰጣል፡፡

22.የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. በክልሉ ውስጥ ህግና ስርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
2. ወንጀል እንዳይፈፀም አስቀድሞ በመከላከል የክልሉን ህዝብ ሰላምና ደህንነት ያስጠብቃል፣ በወንጀል መከላከሉ ተግባር ላይም ህብረተሰቡ ተሳታፊ እንዲሆንና የራሱን ሰላምና ደህንነት

እንዲያስከብር ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

3. የህግ ታራሚዎች የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ በማያውክ ሁኔታ መጠበቃቸውን መመለሳቸውንና ብቁ ዜጐች ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል፣ ለዚሁም ተገቢ እርምጃዎች መውሰዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የህግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ለማጐልበትና በሕገ-መንግስቱም ሆነ በሰብአዊ መብቶች ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ይሰራል፣
5. በክልሉ ውስጥ ከየእርከኑ አስተዳደሮች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
6. ከአጐራባች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ አካባቢዎች የሚነሱ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የማፈቱበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣
7. የክልሉን ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን በማረጋገጥ ረገድ አግባብ ካላቸው ክፍሎች ጋር ተባብሮ ይሰራል፣ በአስተዳደራዊ ውስኖች፣ በህዝብ ደህንነትና በፀጥታ ሥራ ጉዳዮች ረገድ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግስትና የሌሎች ክፍሎች አካላት ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፡፡

23.<u>የማስታወቂያ ቢሮ</u>

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማስታወቂያ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የክልሉን መንግስት ፖሊሲዎችንና ኘሮግራሞች ለህዝብ ያስተዋውቃል፣ ወቅታዊ የመንግስት መረጃዎችን ያሰራጫል፣ ለዚህም የሚያስፈልገውን ስርዓት ይዘረጋል፣ የመራል፣
2. ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉ እና የክልሉን መልካም ገፅታ የሚያጐለብቱ የሚዲያ ኘሮግራሞች እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደርጋል፣
3. ለህብረተሰቡ መድረስ የሚገባቸው መረጃዎች በወቅቱና በትክክል የሚደርሱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ በክልሉ ውስጥ ኋላቀርና ልማት አደናቃፊ ወጐች፣ አመለካከቶችና እምነቶች ተወግደው ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር የሚያስፈልጉ መድረኮችን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ያዘጋጃል፣
4. በክልሉ ውስጥ ኋላቀርና ልማት አደናቃፊ ወጐች አመለካከቶችንና እምነቶች ተወግደው ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር የሚያስፈልጉ

መድረኮችን በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ያዘጋጃል፡፡

5. በክልሉ ውስጥ ልዩ ልዩ የዜናና የመረጃ አውታሮች የሚዘገብበትንና የሚስፋፊበትን ስልት ይቀይሳል፣
6. ከክልል ወደ ፌዴራልና ከፌዴራል ወደ ክልል የሚደረጉትን የኢንፎርሜሽን፣ የዜናና የኘሮግራም ልውውጦች በማስተባበር ረገድ አስፈላጊውን ይፈፅማል፣ ከሌሎች ክልሎች አቻ ተቋማት እና ከሚመለከታቸው መሰል አካላት ጋር የልምድ እና የተሞክሮ ልውውጥ የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
7. ስርጭታቸው በክልሉ ውስጥ ብቻ የሆነና ትርፍ ለማግኘት የሚውጠ ጋዜጦችን፣ መፅሔቶችንና በራሪ ፅሁፎችን ለሚያሳትሙ ሰዎችና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡

24.የውሃ ሀብት ልማት ቢሮ

በሌሎች ህጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የውሃ ሀብት ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የውሃ ሀብት አስተዳደርን በሚመለከት በፌዴራሉና በክልሉ መንግስታት የወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ተፋሰሶችና ንዑሳን ተፋሰሶች የውሃ ሀብት ክምችና ስርጭት ያጠናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይይዛል፣ ይተነትሃል፣ በወቅቱ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፣ ከሌሎች ጋር በመተባበር በሚካሄዱ ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፡፡
3. የክልሉ የውሃ ሃብት አስተዳደር ሁለንተናዊ አቅም በሚገባ ተገንብቶ በቅነጅት እንዲከናወን የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኘው የውሃ ሃብት በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና በጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፡፡
5. የጥናትና ምርምር ኘሮጀክቶችን ጨምሮ የክልሉን የውሃ ሃብት በሚመለከት የውሃ ጉዳጊዶችን ለመቆፈር፣ የተፋሰስ ልማት ስራዎተን፣ የፍሳሽ ማስወገድ ወይም የድሬኔጅና የመስኖ እንዲሁም የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦችንና ሌሎች የውሃ ስራዎችን ለመገንባት፣ ለመጠገንና በጥቅም ላይ ለማዋል ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመከባበር ፈቃድ ይሰጣል፣

ያድሳል፣ ይሰርዛል፡፡

6. የውሃ ስራዎችን በተመለከተ በራሱ አነሳሽነትም ሆነ አግባብ ባላቸው አካላት ጠያቂ ሲቀርብለት ዲዛየኖችን ይሠራል፣ እንዲሰሩ የደርጋል፣ በመስኩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫና በውሃ አካላት የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፣ ለዚሁም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣
7. የክልሉን የውሃ ታሪፍና የወጭ አመላለስ በተመለከተ ወጥና ፍትሃዊነት ያለው የታሪፍ የወጭ ተመላሽ አወሳሰን ሥርዓት ተቀርፆ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ጥናቶችን ያካሂዳል እንዲካሄዱም ያደርጋል፡፡
8. በክልሉ ውስጥ ለልሉ ለዩ ግልጋሎቶች ለሚውል ውሃ የተወሰነው የጥራት ደረጃ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ፍሳሾች የተወሰነው የጤናማነት ደረጃ መጠበቁንና በስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በፊዚካል፣ በኬሚካል፣ በባዮሎጅካል በባቴሪዮሎጅካል እና በራደሎጅካል የምርመራ ዘዴዎች ተጠቅሞ ፍተሻ በማካሄድ ውሃው እንዲታከም ያደርጋል፡፡
9. የሜትሮሎጅና የሃድሮሎጅ መረጃዎተን ከሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ በመተንተንና በማሰራጨት ለልማት ሥራ እንዲውል ያደርጋል፣
10. የውሃ ሃብትን በመጠበቅ ረገድ በተለይም ክልል ዘለል የሆኑ የውሃ አካላትን በሚመለከትና በክልሉ ውስጥ በፌዴራል መስሪያ ቤቶች አማካይነት ለሚካሄዱ ስራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
11. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውሃ አካላት ዳርቻዎች እንዲከለሉና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣
12. የውሃ ሀብት አስተዳደርን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎተን፣ ስትራቴጅካዊ እቅዶችን መመሪያዎችን፣ ስታንዳርዶችንና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሠራጫል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡
13. የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ከሣኒቴሽን ስራዎች ጋር ተቀናጅቶ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
14. በውሃ ሃብት ዘርፍ በምርምር ሥራዎች ይሳተፋል፣ የምርምር ውጤቶች በሠርቶ ማሳያ ዘዴዎች እንዲታወቁና በልማት ላይ እንዲውሉ ያበረታታል፣ የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ ለማገዝ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡
15. የውሃ አጠቃቀም መብቶች ይከበሩ ዘንድ በውሃ

ሃብት ይዞታና አጠቃቀም ረገድ የሚነሱ ግጭቶችና ክርክሮች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፣ የባለመብትነት ጥያቄዎችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፣

16. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውሃ ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ዘላቂና ተፈላጊ አገልግሎት ይሰጡ ዘንድ በኦኘሬሽንና ለጥገና ስራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ድርጅታዊ አቅማቸው የሚጐለብትበትንና የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የሚጠናከሩበትን ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፣
17. በውሃ አካላት ላይ የሚደረገውን ህገ-ወጥ የልማት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አስጊ የቆሻሻ ክምችት እንዳይፈፀሙና የውገ ብክለት እንዳይደርስ የኘሮጀክት ሃሳቦችን በመገምገም ተስማሚ የሆኑትን ያፀድቃል፣ የውሃ አካላት ደህንነት መጠበቁንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

25. <u>የወጣቶችና ስፖርት ጉደይ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ ወጣቶች በነፃ ፍላጐታቸው ተደራጅተው በሀገሪቱ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ መልካም አስተዳደርና ልማት አንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣
2. የወጣቶች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣
3. በክልሉ ውስጥ የተደራጁ ወጣቶች በማያካሂዱት ሥራ ፈጣሪነትን የማጐልበት እንቅስቃሴ ረገድ ተገቢውን የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፣
4. ወጣቶችን በተመለከተ የሚወጡ አገር አቀፍ ፖሊሲዎች በክልሉ ውስጥ ስለመፈፀማቸው ይከታተላል፣ በዘርፉ የተለያዩ አካላት የሚደርጓቸውን እንቅስቃሴዎተ ያስተባብራል፣
5. በክልል አቀፍ ደረጃ ጤናማና ኃላፊነት የሚሰማው የወጣት ኃይል ለማፍራት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣
6. የክልሉ ወጣት የክልሉንና የአገሪቱን ብሔረሰብ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህልና ታሪክ እንዲያውቅ እንዲያከብር፣ እንዲጠብቅ፣ እንዲንከባከብና

እንዲያዳብር ያበረታታል፣

7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን ወጣት ሁለንተናዊ ስብዕና ለማዳበር የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፣
8. በወጣቶች ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራት ሁሉን አቀፍ ሆነው የሚቀናጁበትና ፋይዳቸው የማገመገምበት የቢሮዎች ጥምረት ይመሰረታል፣ ሥራውን ይከታተላል፣
9. ስፖርትን በተመለከተ የሚወጡ አገር አቀፍ ፖሊሲዎች በክልሉ ውስጥ በተክክል መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣
10. በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ለሚቁቁሙ የስፖርት ማህበራት ፈቃድ ይሰጣል፣ ኘሮግራምቻቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
11. ክልላዊ የስፖርት ውድድሮችን ያዘጋጃለ እንዲዘጋጁ ፈቃድ ይሰጣል፣
12. ክልላዊ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማህበራት መካከል የሚነሱ ክርክሮችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፣
13. የክልሉን የስፖርት ምክር ቤት ያቋቁማል፣
14. የክልሉን ባህላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁ፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣
15. የክልሉን ስፖርት ማህበራት የሚሰበሰቡት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፣
16. በክልሉ ውስጥ የስፖርታዊ ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣
17. ከክልሉ የጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ የህክምና አገልግሎቶችን ያዘጋጃል፣
18. ህብረተሰቡ በስፖርቱ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ አስፈላጊውን ስልት ይቀይሳል።

26. <u>የሴቶች ጉዳይ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ የሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣
2. በክልሉ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጐች የልማት ኘሮግራሞች

ኘሮጀክቶች፣ እቅዶች እና ሪፖርቶች የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ ለማካተት የሚያስችላቸውን ስልት በመንደፍ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ተፈፃሚነቱንም ያረጋግጣል፣

3. የሴቶች በክልሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው እድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችንና የሚፈፀሙ ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት እነዚሁ የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል።
5. ሴቶች ለዘመናለት በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ሃሳብ ያቀርባል። ተግባራዊነንም የከታተላል።
6. የተለያዩ የክልሉ የመንግስት አካላት ሴቶችን በውሳኔ ሰጪ ቦታዎች በመመደቡ ረገድ በቂ ትኩረት ስለመስጠታቸው ይከታተላል።
7. ሴቶች እንደፍላጐታቸውና እንደየችግሮቻቸው አይነት ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
8. ብሔራዊው የሴቶች ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን በክልል አቀፍ ደረጃ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
9. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ያስጠናል፣ ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ለዚሁ ዓላማ ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል።
10. የእናቶችና የህዝናት ደህንነት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ያጠናል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
11. መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከተለያዩ የማህበረሰብ ተቋማትና ከሴቶች ማህበራት ጋር ሴቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ተባብሮ ይሠራል፣
12. የፆታ እኩልነትን ለማስፈን፣ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጐልበትና ህብረተሰቡ በሴቶች ላይ ያለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ለመቀየር የሚረዱ

ስልጠናዎችንና ዓውደ ጥናቶች ያካሂዳል፣ ውጤታቸውንም ይገግማል፣

13. ሴቶች በክልሉ ውስጥበሚሰጡ የሥራ ቅጥር፣ የስልጠናና የደረጃ እድገት እድሎችም ሆነ እነዚህኑ ለማስፈፀም በሚደራጁ የተለያዩ ኮሚቴዎች በሚገባ መወከላቸውን ይከታተላል፡፡
14. ሴቶችን ለሚያግዙና ለክልሉ ልማት አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ ኘሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል እርዳታ ያፈላልጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እርዳታው የክልሉን ሴቶች ህይወት ለማሻሻል መዋሉንና ውጤታማነቱን ይከታተላል፡፡

27. <u>ባህልና ቱሪዝም</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወየም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በባህል ተፅእኖ ሳቢያ የክልሉን ማህበራዊ እድገት የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባራት ያከናውናል፣
2. የባህሉ ዘርፍ ልማታዊ አስተዋፅኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
3. በባህል ዘርፍ የህዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡
4. ባህል ኪነ-ጥበብ ሥነጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
5. በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ተፈልገው እንዲገኙ እንዲጠበቁ፣ እንዲጠኑ፣ እንዲታደሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡ ቅርሶችንና በመጥፋት ላይ ያሉ ባህሎችን ከዝርዝር መግለጫ ጋር ይመዘገባል፣
6. በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ ማህበር ወይም የሀይማኖች ድርጅት ወይም ተቋም እጅ የሚገኙ ቅርሶች በሚገባ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ድጋፍ ይሰጣል፣
7. በክልሉ ውስጥ የህዝብ ቤተ-መፅሐፍት፣ ቤተ-መዛግብትና አብያተ መዘክሮች /ሙዚየሞች/ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
8. በክልሉ የፊልምና የቲያትር ቤቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡ የህብረተሰቡን ባህል ታሪክና ሥነ-ምግባር ጠብቀው መካሄዳቸውንም ይቆጣጠራል፣
9. የክልሉ ብሔር-ብሔረሰቦችና ህዝቦች ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ቋንቋቻቸውም እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

10.የክልሉን የባህልና የቱሪዝም መማክርት ጉባኤዎችን ያቋቁማል፡፡
11.ከሚመለከታቸው የክልሉ መነግስት አካላት ጋር በመተባበር በየደረጃው የስነ-ጥበብ ትጥቅና መሣሪያዎች እንዲሟሉ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፣
12.አግባብነት ካላቸውና በየደረጃው ከሚገኙ የክልል መስተዳድር አካላትና መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ካልሆነ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶ ጋር በመተባበር የክልሉን የቱሪስት መስህብ ሀብቶች ያጠናል፣ ይመዘግባል፣ እንዲደራጁና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
13.አስቀድመው በሚደረጉ የገበያ ጥናቶች መሠረት የክልሉን የቱሪስት መስህብ ሀብቶች በተለያዩ ዘዴዎች በማስተዋወቅ የአገር ውስጥና የውጭ ቱሪዝምን ያስፋፋል፣
14.በክልሉ ውስጥ ቱሪዝም ነክ-የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፣
15.የአካባቢ አስጐብኝዎች በስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያሰለጥናል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ በክልሉ ውስጥ አኩሪ የቱሪዝም ባህል እንዲዳብር ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል፣
16.የሀገሪቱን የቱሪዝም ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የግል ባለሀብቶች በቱሪዝሙ ዘርፍ በንቃትና በስፋት እንዲሳተፉና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የማህበረሰብ ቱሪዝም የሚያድግበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
17.የክልሉ ውስጥ በባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶና ተቋማት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣
18.የቱሪት አገልግሎት ሰጭ ድርጅትና ተቋማት ደረጃቸውን ጠብቀው ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
19.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና ሌሎች የአካባቢ ልማት ስራዎች ቱሪዝምን ባካተተ መንገድ እንዲካሄዱ የበኩሉን ክትትል ያደርጋል፣
20.ቱሪዝም ነክ የሆኑ የተለያዩ የማስፈፀሚያ ደንቦችና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ተፈፃሚነታቸውን ይከታተላል፡፡
21.ቱሪዝም ነክ በሆነ ጉዳዮች ላይ አግባብ ያላቸውን

አካላት ሥራ ያስተባብራል፣ ግንኙቶችን ያደርጋል፣

22.በክልሉ ውስጥ የቱሪዝም እድገትን ለማፋጠን የክፍለ ኢኮኖሚውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡

28.<u>የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጐች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሀገሪቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎችና ህጐች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
2. አሰሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣
3. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የስራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣
4. በብሔራዊ ክልሉ የግዛት ውስጥ በየድርጅቱ የሚቋቋሙትን የሠራተኛና አሰሪ ማህበራት ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
5. የህብረት ስምምነት ድርድሮችና የስራ ክርክሮች በህግ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍፃሜ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፣ የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፡፡
6. አግባብ ካላዠው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ስጥ በስራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና በስራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለሙያው አመዳደብ ጠናት ያደርጋል፣
7. በክልሉ ውስጥ ሠራ ፈላጊዎችና ክፍት የስራ መደቦች እንዲመዘገቡና ሥራና ሰራተኛ እንዲገናኙ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
8. ስለክልሉ የሰው ኃይልና የሥራ ስምሪት ለሠራተኞች ደህንነትና ጤና እንዲሁም አሰሪና ሠራተኛን ስለሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ከትንተና ጋር ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣
9. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ኘሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
10. የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን

ህብረተሰብ ጥረት ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

11. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብና የህፃናት ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የጋብቻ ስርዓትን ለመንከባከብ የውጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

29. <u>ስለሌሎች የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት፣</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተደረጉት የስያሜና የተጠሪነት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት በየተቋቋሙባቸው ህጐች በተደነገገው መሠረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡
2. የክልሉን መንግስት አስፈፃሚ አካላትና ኃላፊዎቻቸውን በሚመለከት ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ የተመለከተው የስያሜ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ የስያሜ ማሻሻያው በአስፈፃሚ አካላቱ የተጠሪነት ደረጃ እንዲሁም መብቶችና ግዴታዎች ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አይኖረውም፡፡
3. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ይሆናል፡1
   ሀ. ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
   ለ. የሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት
   ሐ. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና የሥልጠና ማስፋፊያ ኤጀንሲ፡፡
4. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡
   ሀ. የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት፣
   ለ. የህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ
   ሐ. የገጠር ኢነርጅና የማዕድን ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣
   መ. የምግብ ዋስትና ኘሮግራሞች ማስተባበሪያና የአደጋ መከላከልና ዝግኙት ጽ/ቤት
5. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል፡-
   ሀ. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣
   ለ. የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ኤጀንሲ
   ሐ. የትራንስፖርት ባለስልጣን፣
   መ. የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት፡፡
6. የቤቶች ልማት ድርጅት ተጠሪነቱ ለክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡
7. የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ተጠሪነቱ ለክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ይሆናል፡፡

8. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነቱ ለክልሉ የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ይሆናል፣
   ሀ. የፖሊስ ኮሚሽን
   ለ. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት
   ሐ. የሚሊሻ ጽ/ቤት
9. የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ተጠሪነት ለክልሉ ውሃ ሀብት ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡
10. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ይሆናል፣
   ሀ. የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን
   ለ. የሙሉዓለም ባህል ማዕከል
11. የገቢዎች ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡
12. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት በቀጥታ ለብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተጠሪዎች ይሆናል፡፡
   ሀ. የገጠር መንገዶች ባለስልጣን
   ለ. የአካባቢ ጥበቃና የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለስልጣን፣

30. <u>አስፈፃሚ አካላት በየደረጃው የሚቋሙ ስለመሆኑ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቁሙ የክልል መስተዳድር ም/ቤት አባላት የሆኑ አስፈፃሚ አካላት በክልሉ ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ በየዞኑ መምሪያዎቻቸውን ወይም ተጠሪ ጽ/ቤቶቻቸውን ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብሔረሰብና የወረዳ አስተዳደሮች እንደስማቸው ቅደም ተከተል በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ለሁለገብ ልማትና ለመንግስታዊ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት መምሪያዎችን ወይም ዋና ጽ/ቤቶችን የማቋቁም መብት ይኖራቸዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት የብሔረሰብና የወረዳ አስተዳደሮች መንግስታዊ ተቋማትን ለማደራጀት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚያቀርቡትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ አግባብ ያላቸው የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ አስፈፃሚ አካላት ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት በዞን፣ በብሔረሰብና በወረዳ አስተዳደሮች ውስጥ የሚደራጁ መምሪያዎችና ዋና ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ከየእርከኑ ዋናና ምክትል አስተዳዳሪዎች ጋር በመሆን የየርከኑ አስተዳደር ም/ቤት አባላት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ዝርዝሩ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በሚያወጣው መመሪያ

ይወሰናል፡፡

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

31.የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች፣

1. የሚከተሉት ህጐች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-
   ሀ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/
   ለ. የስፖርት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 10/1988 ዓ.ም
   ሐ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/
   መ. የቱሪዝም ኮሚሽንን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 70/1994 ዓ.ም
   ሠ. የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ ዋጅ ቁጥር 99/1996 ዓ.ም
   ረ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ በድጋሜ ለመወሰን የወጣውን እዋጅ በድጋሜ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 107/1996ዓ.ም
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

32.<u>መብቶችና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ</u>

1. በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ በተናጠል ተቋቁመው የነበሩት የግብርናና የገጠር ልማት ቢሮዎች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ተዋህዶ ለተቋቋመው የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ ተቋቁሞ የነበረው የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ መብቶችና ግዴታዎች እንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙት ለንግድና ኢንዱስትሪ እንዲሁም ለስራና ከተማ ልማት ቢሮዎች ተላልፈዋል፡፡
3. በአዋጅ ቁጥር 90/1995 ዓ.ም የተቋቋመው የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች ምዝገባ፣

ፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ረገድ የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ወደ ተቋቋመው የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

4. በአዋድ 10/1988 ዓ.ም የተቋቋሙ የስፖርት ኮሚሽንና በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ መሠረት የተቋቋመው የወጣቶች ባህልና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ በወጣቶችና በስፖርት ጉዳዮች ረገድ የነበሯቸው መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደ አዲስ ለተቋቋመው የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ተላልፈዋል፡፡
5. በአዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ ተቋቁሞ የነበረው የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የሴቶች ጉዳይ ብሮ ተላልፈዋል፡፡
6. በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም እንደተሻሻለ/ የተቋቁመው የወጣቶች፣ ባህልና ስፖርት እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 70/1994 ዓ.ም የተቋቁመው የቱሪዝም ኮሚሽን የባህልና ቱሪዝም ጉዳዮችን በሚመለከት የነበሯቸው መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ለተቋቁመው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ተላልፈዋል፡፡
7. በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም የተቋቋመውና የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አባል የነበረው የህዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ጉዳዮች ቢሮ በዚህ አዋጅ የፈረሰ ሲሆን መብቶቹና ግዴታዎቹ እንደአግባብነታቸው ወደ ህብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲና በዚህ አዋጅም ሆነ በሌሎች ህጐች ወደ ተቋቁሙት የክልሉ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ተላልፈዋል፡፡

33.<u>***የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፣***</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቁሙት አስፈፃሚ አካላት በሚገባ እስኪደራጁ ድረስ በስራ ላይ ያሉትና አግባብነት ያላቸው ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ለ3 ወራት ያህል ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. /እንደተሻሻለና/ በሌሎች ህጐች ለቀድሞው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተሰጥተው የነበሩት ስልጣንና ተግባራት ከዚህ አዋጅና ከተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተደራጀው ምክር ቤት እንደተሰጡ ተቆጥሮ ይሠራባቸዋል፡፡

34.<u>***ደንቦችን የማውጣት ስልጣን***</u>

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

35. **መመሪያ የማውጣት ስልጣን፣**

የብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ሙሉ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች የማውጣት ስልጣን አለው፡፡

36. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፣**

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡